የብሔራዊ ደም ባንክ አገልግሎት
NATIONAL BLOOD BANK SERVICE

የኢትዮጵያ ደም እና ቲሹ ባንክ አገልግሎት የአፈፃፀም ክትትል እና ግምገማ መምሪያ

(Ethiopian Blood and tissue Bank Service Performance monitoring and evaluation Guide)

ህዳር 2015
አዲስ አባባ

ማውጫ

1. መግቢያ 3
2. በአፈፃፀም ክትትል እና ግምገማ ወቅት የምንከተላቸው መርህዎች 4
3. የአፈፃፀም ክትትል እና ግምገማ አላማ 4
4. የሚሰበሰበው መረጃ ይዘት እና መለኪያዎች 4
5. የመረጃ አሰባሰብ፤ ትንተና እና ስርጭት ዘዴ 7
6. መረጃን ለማሰባሰብ የምንጠቀመው መሳሪያ (Instrument for gathering data) 7
7. የመረጃው ፍሰት (Data flow) 7
8. የአፈፃፀም ክትትል እና ግምገማ ላይ የሚሳተፉ አካላት 8
9. የአፈፃጸም ክትትል እና ግምገማውን ለማካሄድ የሚያስፈልገው ሀብት 10
10. የአፈፃፀም ክትትል እና ግምገማን ለማካሄድ የሚያስፈልገው የጊዜ ሰሌዳ 10
11. በአፈፃጸም ክትትል እና ግምገማ የሚገኘውን መረጃ ለውሳኔ የመጠቀም ሁኔታ 11
12. የስራ አፈጻጸም የውጤት ደረጃ አሰጣጥ (ሚዛናዊ ስኮር ካርድን በመጠቀም) 11

1. መግቢያ

የኢትዮጵያ ደም እና ቲሹ ባንክ አገልግሎት በቂ፤ ደህንነቱ የተረጋገጠ እና በወቅቱ የተዘጋጀ ደም እና የደም ተዋፅኦዎችን እንዲሁም ህብረህዋስ ማሰባሰብ እና የማስተዳደር አገልግሎቶች ለዜጋው ተደራሽ ለማድረግ ታልሞ የተቋቋመ ተቋም ነው፡፡ አገልግሎቱ አገራዊ ሀብት የሆነው ደም በብሄራዊ ደረጃ በቂ ክምችት መኖሩን ማረጋገጥ፤ ለክልል ደም ባንኮች ተገቢውን ድጋፍ መስጠት እና በትብብር የመስራት ኃላፊነትም በመቋቋሚያ ደንቡ ተሰጥቶታል፡፡ ይህንን የተጣለበትን ከባድ ኃላፊነት ለመወጣት የአስር አመት፤ የአምስት አመት እና አመታዊ እቅድ በማቀድ በመተግበር ላይ የሚገኝ ሲሆን አፈፃጸሙን ለማሻሻል እና ውጤት ለማስመዝገብ የተለያዩ ስትራተጂዎችን እየተከተለ ይገኛል፡፡ ውጤት ለማምጣት ትኩረት ተሰጥቷቸው ሊከናወኑ ከሚገባቸው ተግባራት አንዱ የአፈፃፀም ክትትል እና ግምገማ ነው፡፡ የአፈፃፀም ክትትል እና ግምገማ የተቋሙን ዕቅድ ከትግበራ አፈጻጸም ጋር በማነጻጸር ክፍተት የሚፈተሽበትና የሚጠበቁ ውጤቶች መገኘታቸው የሚያረጋግጥበት ሥርዓት ሲሆን ቀጣይነት ባለው መልኩ መከወን ይገባዋል፡፡ በመሆኑም የኢትዮጵያ ደም እና ቲሹ ባንክ አገልግሎት የአፈፃጸም ክትትል እና ግምገማ ስርኣቱን የተቀላጠፈ ለማድረግ አለም አቀፍ የደም ደህንነት መረጃ ቋትን (Global data base blood safty) መሰረት ያደረገ መለኪያዎችን በማውጣት በዲጂታል ቴክኖሎጂ በመታገዝ መረጃን ለመሰብሰብ እና ለመተንተን እንዲሁም የግብረ መልስ ስርዓት ለመፍጠር እና መረጃ ላይ መሰረት ያደረገ ውሳኔ መስጠት እንዲቻል የአፈጻጸም ክትትል እና ግምገማ ቡድን በማቋቋም ስራውን በተቀላጠፈ መንገድ ለመከወን ያቀደ ሲሆን ይህ መምሪያም የአፈፃፀም ክትትል እና ግምገማ ቡድን የአሰራር ስርዓትን ለመደንገግ የተዘጋጀ ነው፡፡

2. በአፈፃፀም ክትትል እና ግምገማ ወቅት የምንከተላቸው መርህዎች

የአፈፃፀም ግምገማው እና ክትትሉ ስኬታማ እንዲሆን የሚከተሉትን መርሆዎችን መከተል አለበት፡-

2.1. ግልጽነት

2.2. አሳታፊነት

2.3. ወቅታዊነት

2.4. ሚዛናዊነት

3. የአፈፃፀም ክትትል እና ግምገማ አላማ

3.1. የደም ባንኮች አፈፃጸም ከታቀደው አንፃር ውጤታማ መሆኑን እና አለመሆኑን ለመገንዘብ እና ተገቢውን የመደጋገፍ ስራ ለመስራት

3.2. በአፈጻጸም ወቅት የታዩ ክፍተቶችን እና ፈታኝ ሁኔታዎችን ለመለየት፣ እንዲሁም በቀጣይነት የማስተካከያ እርምጃዎችን ለመውሰድ፣

3.3. የተለያዩ ፈጻሚ አካላትን በአፈጻጸም ውጤታቸው መሠረት ለማበረታታትና እውቅና ለመስጠት፣

3.4. ለሚቀጥለው የዕቅድ ዘመን ቀረጻ ግብአት የሚሆኑ ጉዳዮችን ለመለየት እና ለመጠቀም፣

4. የሚሰበሰበው መረጃ ይዘት እና መለኪያዎች

የደም ባንክ አገልግሎትን ተልዕኮ እና ራዕይ የስኬት ደረጃን መመዘን እንዲቻል መለኪያዎችንና ዒላማዎችን መለየት እና መለኪያዎችንና ኢላማዎችን መመዘን የሚያስችል መረጃን ማሰባሰብ ወሳኝ ተግባር ነው፡፡ ከዚህ አንፃር የኢትዮጵያ ደም እና ቲሹ ባንክ አገልግሎት የአስር አመት እና የአምስት አመት እስትራተጂክ እቅድ ያዘጋጀ ሲሆን የርዕይ እና የተልዕኮ ስኬትን መመዘን የሚያስችል አላማ፤ እስትራተጂክ አቅጣጫ፤ መለኪያ እና ዒላማን የመለየት ስራ ተሰርቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የአለም የመረጃ ቋት ውስጥ የተካተቱ የአለም ጤና ድርጅት የሚጠቀማቸውን የደም ባንክ አገልግሎት አፈፃፀምን የሚለኩ መለኪያዎችን የያዘ ዲጂታል ስርዓት መፍጠር ተችሏል፡፡ ስለሆነም የሚሰበሰበው የመረጃ ይዘት መነሻ የሚያደርገው የተቋሙን እስትራተጂክ እቅድ እና የአለም የመረጃ ቋት ውስጥ የተካተቱ የደም ባንክ አገልግሎት

መለኪያዎችን ሲሆን መረጃዎቹ የደም ልገሳ አገልግሎት፤ የላብራቶሪ አገልግሎት፤ የሜዲካል አገልግሎት እና ጥራት እና ደህንነት አገልግሎት የሚመለከቱ ናቸው፡፡

4.1. የአፈፃጸም ክትትል እና ግምገማ ለማካሄድ አገልግሎት ላይ የሚውሉ ወሳኝ የአፈፀም መለኪያዎች

ወሳኝ የአፈፃፀም መለኪያዎች
1. በአጠቃላይ የተሰበሰበው ደም መጠን (Total collection performance)
2. ከበጎ ፈቃደኛ ደም ለጋሾች የተሰበሰበው ደም በመቶኛ (Percentage of blood collected from volunteers)
3. በተንቀሳቃሽ ቡድን የሚሰበሰብ አማካይ የደም መጠን በዩኒት(Average unit of blood per mobile session)
4. በድግግሞሽ ደም ከሚለግሱ የተገኘ ደም በመቶኛ (Percentage Blood donation from repeat donors)
5. ከማዕከል የተሰበሰበ ደም በመቶኛ (Percentage of center collection)
6. ከደም ልገሳ ጋር በተያያዘ ያጋጠመ የጤና መታወክ ክፋይ (Proportion of ADE related to donation)
7. በተለያየ ምክኒያት ደም መለገስ ባለመቻል ለሌላ ጊዜ የተላለፈ ክፋይ (Proportion of total deferral)
8. የድህረ ደም ልገሳ አገልግሎት ያገኙ ለጋሾች በመቶኛ(Percentage of donors who received PDC service)
9. በደም ህክምና የሚተላለፉ በሽታዎች የተገኘባቸው እና ውጤታቸውን ያወቁ ለጋሾች በመቶኛ (TTIs positive who know their TTIs status)
10. በደም ህክምና የሚተላለፉ በሽታዎች የተገኘባቸው እና ከጤና ተቋማት ህክምና አገልግሎት እንዲያገኙ የተደረጉ ለጋሾች በመቶኛ (Percentage of donors TTIs positive who referral linked with health facility)
11. የደም ተዋፅኦ የተዘጋጀበት ደም ክፋይ (Proportion of WB separated into components)
12. በደም ህክምና ለሚተላለፉ በሽታዎች በአጠቃላ የተደረገ ምርመራ (Total number of TTIs screening)
13. የጥራት ማረጋገጫ በመቶኛ (Percentage of quality-assurance)
14. በደም ህክምና የሚተላለፉ በሽታዎች የተገኘባቸው ለጋሾች (Total number of Donors positive for TTIS)
15. በደም ህክምና የሚተላለፉ በሽታዎች የተገኘበት ደም በመቶኛ (Percentage of TTIs positive)
16. ኤች አይ ቪ በደማቸው የተገኘ በመቶኛ (Percentage of HIV positive)
17. ሄፓታይተስ ቢ በደማቸው የተገኘ በመቶኛ (Percentage of Hepatitis B positive)
18. ሄፓታይተስ ሲ በደማቸው የተገኘ በመቶኛ (Percentage of Hepatitis C positive)
19. ቂጥኝ በሽታ በደማቸው የተገኘ በመቶኛ (Percentage of Syphilis positive)
20. የተወገደ የደም ተዋፅኦ ያልወጣለት ደም/ቀይ የደም ህዋስ መጠን (Wastage rate of WB/CRC)
21. በደም ማሰባሰብ ሂደት ውስጥ በተፈጠረ ችግር የተወገደ ደም በመቶኛ (Percentage of discarded units due to collection problem from the total discard)
22. በተዋፅኦ ዝግጅት ሂደት በተፈጠረ ችግር የተወገደ የደም ተዋፅኦ ያልወጣለት ሙሉ ደም/ቀይ የደም ህዋስ በመቶኛ

(Percentage of discarded units of WB/CRC due to processing problem from the total discard)

23. የመጠቀሚያ ጊዜው በማለፉ የተወገደ የደም ተዋፅኦ ያልወጣለት ሙሉ ደም/ቀይ የደም ህዋስ በመቶኛ (Percentage of discarded units of WB/CRC by passed the expiry date from the total discard)
24. በደም ህክምና የሚተላለፉ በስታዎች ስለተገኙበት የተወገደ የደም ተዋፅኦ ያልወጣለት ሙሉ ደም/ቀይ የደም ህዋስ በመቶኛ (Percentage of discarded units of WB/CRC by reactive for TTIs/Infectious Disease from the total discard)
25. የደም ህዋሳት በመሞታቸው ምክኒያት የተወገደ የደም ተዋፅኦ ያልወጣለት ሙሉ ደም/ቀይ የደም ህዋስ በመቶኛ (Percentage of discarded units of WB/CRC by Hemolyzed from the total discard)
26. የደም መርጋት በማጋጠሙ የተወገደ የደም ተዋፅኦ ያልወጣለት ሙሉ ደም/ቀይ የደም ህዋስ በመቶኛ (Percentage of discarded units of WB/CRC by Clotted from the total discard)
27. በማከማቻ ችግር የተወገደ የደም ተዋፅኦ ያልወጣለት ደም/ቀይ የደም ህዋስ በመቶኛ (Percentage of discarded units of WB/CRC by storage problems from the total discard)
28. በመጓጓዣ ችግር የተወገደ የደም ተዋፅኦ ያልወጣለት ሙሉ ደም/ቀይ የደም ህዋስ በመቶኛ (Percentage of discarded units of WB/CRC by transportation problems from the total discard)
29. በደም የሚተላለፍ በሽታን በመጠራጠር የተወገደ የደም ተዋፅኦ ያልወጣለት ሙሉ ደም/ቀይ የደም ህዋስ በመቶኛ (Percentage of discarded units of WB/CRC by high OD from the total discard)
30. በሌሎች ምክኒያቶች የተወገደ የደም ተዋፅኦ ያልወጣለት ሙሉ ደም/ቀይ የደም ህዋስ በመቶኛ (Percentage of discarded units of WB/CRC by others from the total discard)
31. በተዋጽኦ ዝግጅት ወቅት በተፈጠረ ችግር ምክኒያት የተወገደ ፕሌትሌት በመቶኛ (Percentage of discarded units of platelet due to processing problem)
32. በተዋጽኦ ዝግጅት ወቅት በተፈጠረ ችግር ምክኒያት የተወገደ ፕላዝማ በመቶኛ (Percentage of discarded units of FFP due to processing problem)
33. የጤና ተቋማት የደም ፍላጎት እርካታ መጠን (Health facilities blood satisfaction rate)
34. የሆስፒታል የደም ህክምና ኮሚቴ ያላቸው የጤና ተቋማት በመቶኛ (Percentage of HFs that have HTC)
35. ስራ ላይ የሚገኙ የሆስፒታል የደም ህክምና ኮሚቴ ክፋይ (Proportion of functional HTC which perform clinical)
36. የደም ህክምና ያገኙ ታካሚዎች በመቶኛ (Percentage of Transfusion)
37. ስራ ላይ ያለ የደም ለጋሽ ክለብ በቁጥር (Total Number of active blood donors Club)
38. የደም ማስተላለፍ ህክምና የሚሰጡ ተቋማት በቁጥር (Number of HFs that perform blood transfusion)
39. የድህረ ደም ልገሳ አገልግሎት የሚሰጡ ደም ባንኮች በቁጥር(Number of blood banks have a service of PDC)

40. የደም ተዋፅኦ ዝግጅት አገልግሎት የሚሰጡ የደም ባንኮች በቁጥር (Number of blood banks have a service of component production)

5. የመረጃ አሰባሰብ፤ ትንተና እና ስርጭት ዘዴ

መረጃው የሚሰበሰበው በሁሉም ደም ባንኮች ለደም ማሰባሰብ፤ ለምርመራ፤ ለሜዲካል አገልግሎት እና ለምክር አገልግሎት የምንጠቀማቸውን ፎርማቶች በተገቢው መንገድ በመሙላት እና በመጠቀም ሲሆን ቢ ኤስ አይ ኤስ እየተገበሩ ያሉ ተቋማት ቢኤስ አይ ኤስን ለመረጃ ምንጭነት ሊጠቀሙ የሚችሉ ሲሆን ሌሎች የመረጃ ምንጮችም ተገቢ መረጃ ማመንጨት እስከቻሉ ድረስ አገልግሎት ላይ ሊውሉ ይችላሉ፡፡ የተሰበሰበውን መረጃ ሁሉም ደም ባንኮች በተዘጋጀው ዲጂታል መሳሪያ (eVVrt) በመሙላት ለኢትዮጵያ ደም እና ቲሹ ባንክ መላክ ይገባቸዋል፡፡ የኢትዮጵያ ደም እና ቲሹ ባንክ አገልግሎትም መረጃውን ከክልል ደም ባንኮች የሚሰበስብ የሰው ሀይል በመመደብ መረጃውን ይቀበላል፡፡ የተቀበለውን መረጃ የሚተነትን ቡድን በማቋቋም ጥልቅ ትንተና በማድረግ ለበላይ አመራር እና ለማኔጅመንት ካውንስል እንዲቀርብ ያደርጋል፡፡ ማኔጅመንት ካውንስሉ የተተነተነውን ሪፖርት ገምግሞ ግብረ መልስ ለሁሉም ደም ባንኮች እንዲሰጥ ያደርጋል፡፡

6. መረጃን ለማሰባሰብ የምንጠቀመው መሳሪያ (Instrument for gathering data)

ለመረጃ ማሰባሰብ ስራ የምንጠቀመው መሳሪያ የደም ባንክ የመረጃ ፎርማቶች እና የኤሌክትሮኒክ ቬን ቱ ቬን ሪፖርቲንግ ቱልን (eVVrt) ሲሆን ቢ ኤስ አይ ኤስም (BSIS) እንደ አስፈላጊነቱ አገልግሎት ላይ እንዲውል ይደረጋል፡፡

7. የመረጃው ፍሰት (Data flow)

መረጃ በዋናነት የደም ማሰባሰብ፤ ምርመራ እና ተዋፅኦ ዝግጅት እንዲሁም የደም ህክምና ከሚሰጡ ተቋማት እና ደም ባንኮች ይገኛል፡፡ ደም ባንኮች መረጃውን ከላይ ከጠቀስናቸው ምንጮች ሰብስበው በቬን ቱ ቬን ሪፖርቲንግ ቱል (eVVrt) ለብሄራዊ ደም ባንክ እንዲልኩ ይደረጋል፡፡ የብሄራዊ ደም በንክ መረጃውን የሚያሰባስብ፤ የሚተነትን እና ለማኔጅመንት ካውንስል የሚያቀርብ የሰው ሀይል የሚመድብ ሲሆን ማኔጅመንት ካውንስሉ የቀረበለትን የተተነተነ መረጃ በመገምገም ለክልል ደም ባንኮች እና ለክልል ጤና ቢሮዎች እንዲሁም ለጤና ሚኒስቴር እንዲያውቁት ሪፖርት ያደርጋል፡፡ የክልል ጤና ቢሮ እና ጤና ሚኒስቴርም

በሚቀርብላቸው መረጃ መነሻነት ተገቢውን ክትትል እና ድጋፍ እንዲሁም የእርምት እርምጃዎችን ይወስዳሉ፡፡

8. የአፈፃፀም ክትትል እና ግምገማ አደረጃጀት

በኢትዮጵያ ደም እና ቲሹ ባንክ ደረጃ ከክልሎች መረጃ የሚሰበስብ ቡድን ከእቅድ ዝግጅት፤ ክትትል እና ግምገማ ዳይሬክቶሬት ይቋቋማል፡፡

የተሰበሰበውን መረጃ በመተንተን እና በማደራጀት እንዲሁም የባላንስድ እስኮር ካርድን በመጠቀም አፈጻጸሙን በማወዳደር እና ደረጃ በማውጣት ለተቋሙ የበላይ አመራር እና ለማኔጅምንት ካውንስል የሚያቀርብ **የአፈፃጸም ክትትል እና ግምገማ ቡድን** እንደሚከተለው ተቋቁሟል፡፡

- የእስትራተጂክ ጉዳዮች ስራ አስፈፃሚ---ሰብሳቢ
- የደም ለጋሾች አገልግሎት መሪ ስራ አስፈፃሚ/ተወካይ---አባል
- የላብራቶሪ አገልግሎት መሪ ስራ አስፈፃሚ/ተወካይ----አባል
- የሜዲካል አገልግሎት መሪ ስራ አስፈፃሚ/ተወካይ----አባል
- የጥራት እና ደህንነት አገልግሎት መሪ ስራ አስፈፃሚ/ተወካይ-----አባል
- የአለም ጤና ድርጅት የደም ባንክ አማካሪ---አባል
- የድህረ ደም ልገሳ አገልግሎት ዴስክ ኃላፊ.....አባል
- የትምህርት እና ቅስቀሳ ዴስክ ኃላፊ.....አባል
- የደም ልገሳ ዴስክ ኃላፊ----------አባል
- የደም ተዋጽኦ ዝግጅት ዴስክ ኃላፊ .....አባል
- የመልካም አስተዳደር እና ሪፎርም ስራ አስፈፃሚ/ተወካይ...ፀሀፊ ይሆናሉ፡፡

8.1. የአፈፃፀም ክትትል እና ግምገማ ቡድን አካላት ተግባር እና ኃላፊነት፡

8.1.1. የቡድኑ ተግባር እና ኃላፊነት

- ✓ በእቅድ ባለሙያዎች ከአገሪቱ ደም ባንኮች በየወሩ ተሰብስቦ የቀረበለትን መረጃ ትንተና እና ግምገማ በማካሄድ ለማኔጅመንት ካውንስል ያቀርባል፣
- ✓ ለክልል ደም ባንክ ግብረመልስ ሊሰጥባቸው የሚገቡ ዋና ዋና አመልካቾችን ይለያል፤ በባላንስድ እስኮር ካርድ ለእያንዳንዱ አመልካች ውጤት የሚሰጥበትን ፎርማት ያዘጋጃል፤ እንዲሁም በፎርማቱ መሰረት በየወሩ ግብረ መልስ ያዘጋጃል፡፡

- ✓ የልምድ ልውውጥ በደም ባንኮች መካከል እንዲኖር ኃሳብ ያቀርባል፤ ሲፈቀድ ተግባራዊ ያደርጋል
- ✓ የደም ባንኮች አፈፃፀም ያለበትን ደረጃ ከሪፖርት አንፃር ለማመሳከር በተመረጡ ደም ባንኮች ላይ የድጋፋዊ ክትትል ስራ ይሰራል
- ✓ የክልል ደም ባንኮች እና ደም ማሰባሰቢያ ጣቢያዎች የእውቅና እና ማበረታቻ አሰጣጥ መመሪያ ያዘጋጃል፤ ለማኔጅመንት ካውንስል እንዲሁም ለክልል ደም ባንኮች እና የኢትዮጵያ ደም እና ቲሹ ባንክ አገልግሎት የጋራ አመራር ኮሚቴ እንዲቀርብ በማድረግ ያስፀድቃል፡፡

8.1.2. የሰብሳቢ ተግባር እና ኃላፊነት

- ✓ የቡድኑን ስብሰባ ይመራል
- ✓ ከፀኃፊው ጋር በመሆን የውይይት አጀንዳ ይቀርጻል፤ አጀንዳ ያላቸው የቡድኑ አባላት ካሉ አጀንዳቸውን መርምሮ የአጀንዳው አካል እንዲሆን ያደርጋል
- ✓ ለኮሚቴው የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን ከበላይ አመራሩ በመጠየቅ እንዲሟላ ያደርጋል
- ✓ መረጃ ከክልል ደም ባንኮች እንዲሰበሰብ ያደርጋል፤ መረጃውን ለውይይት በሚያመች መልኩ አደራጅቶ ለቡድኑ ያቀርባል

8.1.3. የፀኃፊው ተግባር እና ኃላፊነት

- ✓ የስብሰባውን ቃለጉባኤ ይይዛል፤ የቡድን አባላቱን በማስፈረም ይሰንዳል
- ✓ ከሰብሳቢው ጋር በመሆን አጀንዳ ይቀርፃል
- ✓ ሰብሳቢው በማይኖርበት ወቅት ሰብሳቢውን ተክቶ የቡድኑን ስብሰባ ይመራል

8.1.4. የቡድን አባላቱ ተግባር እና ኃላፊነት

- ✓ በስብሰባው ላይ በመገኘት የየስራ ክፍላቸውን መረጃ ቴክኒካዊ በሆነ መንገድ ይገመግማሉ፤
- ✓ የተስተዋሉ ክፍተቶች መረጃ ይይዛሉ፤
- ✓ ክፍተቶችን ማስተካከል የሚቻልበትን ዘዴ ይቀይሳሉ፤
- ✓ የድጋፍ እና የክትትል ስርዓት በመንደፍ ድጋፍ ያደርጋሉ

8.1.5. የተቋሙ የበላይ ኃላፊዎች እና ማኔጅመንት ካውንስሉ፡-

- ✓ ከቡድኑ የሚቀርብለትን ሪፖርት ገምግሞ ለሚመለከታቸው አካላት ግብረ መልስ ይሰጣል፡፡
- ✓ ድጋፍ የሚሹ ጉዳዮችን ይለያል፤ ድጋፍ ያደርጋል፡፡

- ✓ የአፈጻጸም ክትትል እና ግምገማ ቡድን ስራውን ለማከናወን የሚያስፈልገውን ግብዓት ያሟላል

8.1.6. የክልል ደም ባንኮች፡

- ✓ eVVrt በመጠቀም በየወሩ ለኢትዮጵያ ደም እና ቲሹ ባንክ አገልግሎት ሪፖርት ይልካሉ፡፡
- ✓ በኢትዮጵያ ደም እና ቲሹ ባንክ አገልግሎት የሚሰጠውን ሪፖርት ግብረ መልስ በመውሰድ አፈጻጸማቸውን ለማሻሻል ይሰራሉ
- ✓ ከአቻ የክልል ደም ባንኮች ጋር በአፈፃጸም የውድድር መንፈስ ይፈጥራሉ፤ ከፍተኛ ውጤት በማግኘት እውቅና እና ማበረታቻ ለማግኘት ይጥራሉ

9. የአፈፃጸም ክትትል እና ግምገማውን ለማካሄድ የሚያስፈልገው ሀብት

በኢትዮጵያ ደም እና ቲሹ ባንክ ደረጃ የአፈፃፀም ክትትሉን እና ግምገማውን ለማድረግ የሚስፈልገው እስቴሽነሪ፤ የኢንተርኔት አገልግሎት፤ ኮሚፒትር አገልግሎት እና መረጃውን ለሚተነትኑ ቡድን አባላት የሚያስፈልጉ መስተንግዶዎች ደንብና መመሪያን በተከተለ መልኩ ለማሟላት ጥረት ይደረጋል፡፡

የክልል ደም ባንኮች ስራውን ለማስኬድ የሚስፈልጋቸውን ሀብት በመለየት እና ከእናት መስሪያበታቸው ማስመደብ ይጠበቅባቸዋል፡፡

10. የአፈፃፀም ክትትል እና ግምገማን ለማካሄድ የሚያስፈልገው የጊዜ ሰሌዳ

የአፈጻጸም ክትትል እና ግምገማ ስራው በየወሩ የሚደረግ ሲሆን በኢቪቪአርቲ በክልል ደም ባንኮች ተሞልቶ ለኢትዮጵያ ደም እና ቲሹ ባንክ የሚመጣው ሪፖርት በፈረንጆች አቆጣጠር ወር በገባ ከ1-5 ቀን ውስጥ ሊደርስ ይገባል፡፡ በዚህ የቀን ገደብ ውስጥ መረጃ ማሰባሰብ ላይ ከላይ የተመደቡ ባለሙያዎች ተሳትፎ ያደርጋሉ፡፡ መረጃው የኢትዮጵያ ደም እና ቲሹ ባንክ አገልግሎት እንደ ደረሰ ወሩ በገባ 6 እስከ 9 ቀን ባለው ጊዜ ውስጥ የአፈፃጸም ክትትል እና ግምገማ ቡድኑ መረጃ በመተንተን እና በማደራጀት እንዲሁም የባላንስድ ስኮር ካርድን በመጠቀም አፈጻጸሙን በማወዳደር እና ደረጃ በማውጣት ለተቋሙ የበላይ አመራር እና ለማኔጅምንት ካውንስል የሚያቀርብ ይሆናል፡፡ የተቋሙ የበላይ አመራር ወር በገባ 12 ቀን ውስጥ በመደበኛ የማኔጅመንት ስብሰባው የቀረበለትን የተተነተነ ሪፖርት በማኔጅመንት በማስገምገም ለሚመለከታቸው አካላት ግብረ መልስ እና የማሳወቅ ስራ መስራት ይኖርበታል፡፡

11. በአፈፃጸም ክትትል እና ግምገማ የሚገኘውን መረጃ ለውሳኔ የመጠቀም ሁኔታ

በአፈፃፀም ክትትል እና ግምገማው የሚገኘውን መረጃ መነሻ በማድረግ አፈፃፀማቸው የተዳከሙትን በመለየት እና ምክኒያቱን በማጥናት ተገቢው ድጋፍ እና ክትትል እንዲደረግላቸው ይደረጋል፡፡ በተከታታይ አፈፃፀማቸው ከፍተኛ የሆኑትን ተቋማት ደግሞ በአመቱ መጨረሻ በሚደረገው የአፈፃፀም ግምገማ ላይ የማበረታቻ ሽልማት እንዲሰጣቸው የሚደረግ ሲሆን አፈፃፀሙ ከሪፖርት በተጨማሪ በድጋፋዊ ጉብኝት በአካል በመገኘት የማረጋገጥ ስራም ይሰራል፡፡ የማበረታቻ ሽልማቱ የአፈፃፀም ደረጃውን እና አቅምን ባገናዘበ መልኩ በኢትዮጵያ ደም እና ቲሹ ባንክ ማኔጅመንት ካውንስል እየተወሰነ የሚሰጥ ይሆናል፡፡

የአፈፃፀም ክትትል እና ግምገማ መረጃውን በተዋረድ ለውሳኔ መጠቀም እንዲቻል የግብረ መልስ እና የሚመለከታቸው ተቋማት እንዲያውቁ የማድረግ ስራም በተከታታይ ይሰራል፡፡

12. የስራ አፈጻጸም የውጤት ደረጃ አሰጣጥ (ሚዛናዊ ስኮር ካርድን በመጠቀም)

I. **ቀይ ቀለም፡-** አፈጻጸሙ ዝቅተኛ መሆኑን የሚጠቁም ነው፡፡ አሁን የደረስንበት አፈጻጸም ከሚጠበቀው መድረሻ (TARGET) አንፃር ከ 55% ከሆነ የምንጠቀመው ቀለም ይሆናል፡፡

II. **ደማቃ ቢጫ ቀለም፡-** መካከለኛ አፈጻጸም መኖሩን የሚጠቁምና አሁን የደረስንበት አፈጻጸም የተሻለ ነገር ግን ከሚጠበቀው መድረሻ አፈጻጸም (TARGET) አንፃር ከ 56%-64% ሲሆን ነው፡፡

III. **ደብዛዛ ቢጫ ቀለም፡-** መካከለኛ አፈጻጸም መኖሩን የሚጠቁምና አሁን የደረስንበት አፈጻጸም የተሻለ ነገር ግን ከሚጠበቀው መድረሻ አፈጻጸም (TARGET) አንፃር ከ65% - 79% ሲሆን ነው፡፡

IV. **አረንጓዴ ቀለም፡-** ጥሩ አፈጻጸም መኖሩን የሚጠቁም ሲሆን አሁን የደረስንበት አፈጻጸም ከሚጠበቀውን መድረሻ (Target) አንፃር ከ 80%- 94% እንዲሁም ከዛ በላይ ማሳካት ሲቻል ነው፡፡

V. **ደማቃ አረንጓዴ ቀለም፡-** ጥሩ አፈጻጸም መኖሩን የሚጠቁም ሲሆን አሁን የደረስንበት አፈጻጸም ከሚጠበቀውን መድረሻ (Target) አንፃር ከ› 95% እንዲሁም ከዛ በላይ ማሳካት ሲቻል ነው፡፡

አቶ ሀብታሙ ታዬ

የኢትዮጵያ ደም እና ቲሹ ባንክ አገልግሎት ም/ዋ ዳይሬክተር